የወ/መ/ቁጥር 161267

የልደታ ምድብ 5ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ እሸቱ ከበደ ሁለታ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ህዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥቅምት 07 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 9፡00 ሰዓት ሲሆሀን በልደታ ክፍለከተማ ቀበሌ 07/14 ክልል ልዩ ቦታው መንዲዳ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ የ61 ዓመት አዛውንት የሆኑት የግል ተበዳይ አቶ ትዕዛዙ ወርቁ የተባሉትን አራት ጊዜ በመደጋገም አፍንጫቸውንና አፋቸው ላይ በመምታት የላይኛው ቋሚ አንድ የፊት ጥርሳቸውን በማነቃነቅ በሰው ሰራሽ መተካት እንዲኖርበት በማድረጉ፤ የላኛው ቋሚ አንድ የፊት ጥርሳቸውና የታችኛው ሁለት ቋሚ ጥርሶቻቸው ስራቸው እንዲጎዳ በማድረጉ በፈፀመው ታስቦ የሚፈፀም ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮች ቀርበው ያስረዱ ሲሆን፤ የግል ተበዳይ ቀኑን እና ዓመተ ምህረቱን እንዲሁም ሰዓቱን አስተካክለው ቦታውንም ጠቅሰው ተከሳሽ አራት ጊዜ በቦክስ እንደመታቸው እና የላይኛው ጥርሳቸው እንዲነቃነቅ በማድረጉ፤ ሌሎች ጥርሳቸውን ቀዝቃዛ ነገርም ሆነ ሙቅ ነገር ሲጠቀሙባቸው እንደሚደነዝዝ እና እንደሚያማቸው፤ ራሳቸውን ጨምሮ እንደሚያማቸው ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፤ ሁለተኛ ምስክር ደግሞ ቀኑን ሳያስተካክሉ ቦታውን ጠቅሰው የግል ተበዳይን ተከሳሽ አራት ጊዜ አፋቸው ላይ በቦክስ ሲመታቸው ማየታቸውንና ጥርሳቸውም መሸረፉን ማየታቸውን አስረድተዋል። በሌላ በኩል ከየካቲት 12 ሆስፒታል የተሰጠ የህክምና ማስረጃ ዐ/ሕግ አያይዞ ያቀረበ ሲሆን፤ የሚገልፀውም የላይኛው ቋሚ አንድ የፊት ጥርስ መነቃነቁን እና በሰው ሰራሽ ጥርስ ሊተካ የሚገባው መሆኑን ሲሆን ፍ/ቤቱም የዐ/ሕግን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ ተከሳስ በክሱ ላይ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀሙ ስለተረጋገጠ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብሎ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዝገበው በወቅቱ ወደ ቤቱ ስገባ መተላለፊያው ጠባብ ነበር፤ በዚህ መንገድ ላይ የግል ተበዳይ አንዳንድ ነገሮችን

ይሸጡና ደሮዎንም እዚያው ቦታ ይዘው ስለነበር፤ መንገዱን እኮ መተላለፊያ አሳጣኸን ብዬ ተነግሬ ገብቼ ስመለስ ተከሳሽ ድንጋይ ይዞ አኔን ለመምታት ሲያሯሩጥ ሸርተት አድርጎት ወድቆ ተጎዳ እንጅ ድርጊቱን አለመፈፀሜን አስረዳለሁ የሚለውን ሲሆን በዚሁ መሰረትም የመከላከያ ምስክሮች ቀርበውና በግልፅ ችሎት መታላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ አቅርቦ ባሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች/ማስረጃው/ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ቀርበው እንዳስረዱት በወቅቱ የግል ተበዳይና ተከሳሽ ሲጣሉ እንደነበር፤ በኋላም የግል ተበዳይ ድንጋይ ይዘው ተከሳሽን ለመምታት ሲሮጡ መውደቃቸውንና ከወደቁበት ሲነሱ አፋቸው አካባቢ ደምቶ እንደነበር መስክረዋል። ይሁን እንጅ መጀመሪያ የግል ተበዳይና ተከሳሽ ፀቡን ሲጀምሩ ያዩ ሳይሆን ድርጊቱ ተፈፅሞ ተበዳይ ድንጋይ ይዘው ወደ ተከሳሽ ሲሮጡና ሲወድቁ ነው። እነዚህ ምስክሮች በወቅቱ ተበዳይ ድንጋይ ይዘው ሲሮጡ ፊት ለፊት ነው የወደቁት በማለት መስክረው ቢሆን ኑሮ ምናልባት ጥርሳቸው አካባቢ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት ሆኗል ሊባል ይችል ነበር፤ ነገር ግን ይህን አላስረዱም። ሌላው የተከሳሽና የግል ተበዳይ የእድሜ ሁኔታ ሲመዘን ተበዳይ በወቅቱ ተከሳሽን በድንጋይ ለመምታት እያሯሯጡ ነበር ለማለት የሚቻል አይደለም። በአጠቃላይ የዐ/ሕግ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች ተከሳሽ የግል ተባይን በቦክስ ደጋግሞ በመምታት በክሱ ላይ የተመለከተውን ጉዳት ያደረሰባቸው መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፤ በተቃራኒው የተከሳሽ ምስክሮች ተከሳሽ ይህን ጉዳት አላደረሰባቸውም በማለት በግልፅ ያላስረዱ በመሆኑ ተከሳሽ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ስር ጥፋተኛ ነው ተብሎ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ ወንጀሉ በፈጸደራል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት
ደረጃ የወጣለት ስለሆነ ፍ/ቤቱ የሚያርምና የሚያስተምር ቅጣት
እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 48 ዓመት ነው፤ ሥራዬ ሹፍርና ነው፤ አምስት ልጆች ያሉኝ
ሲሆን፤ ሁለቱ የ 16 እና 17 ዓመት ልጆች ናቸው፤ ባለቤቴ የመንግስት
ሰራተኛ ስትሆን የወር ገቢዋም ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) ነው፤
የትምህርት ደረጃዬም 9 ኛ ክፍል ነው በማለት አመለክቷል።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የወንጀሉ ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ እርከኑ 6 ነው። የእርከን 6 ፍቅድ ስልጣን ከ 8 ወር እስከ 1 ዓመት ሲሆን ፍ/ቤቱ አስራ አንድ ወርን መነሻ ቅጣት በማድረግ ወስኗል።

ዐ/ሕግ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 መሰረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ እንዳለው ተጠይቆ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ ቅጣቱን አላከበደውም። በሌላ በኩል ተከሳሽ የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ወይም/እና 86 መሰረት በማስረጃ ተደግፎ የቀረበ የቅጣት ማቅለያ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን አላቀለለውም።

በመሆኑም ፍ/ቤቱ ከላይ በተገለፀው እርከን 6 ላይ ያለውን ፍቅድ ስልጣን መሰረት አድርጎ የተከሳሽን የትምህርት ደረጃና የኑሮ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ተከሳሹን ያርመዋል ወደፊትም ያስተምረዋል ብሎ በታመነበት በአስር ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በተከሳሹ ላይ የተወሰነው ቅጣት ከዛሬ ጀምሮ
እንዲያስፈፅም ታዟል። ይፃፍ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ።